# ላይቀር መንደዳቸው

ሐገር ቀብድ ተይዛ ፣ ገንዘብ ተለምኖ
ከኢትዮጵያ ጠላት ፣ ዶላሩ ተጭኖ
ሕዝብን ለማንበርከክ ፣ እውነታን አዳፍኖ
ዜጋ እንዳይተነፍስ ፣ በጉልበት ታፍኖ
መናፍቅ ከሃዲው ፣ ዋቄ ፈታው ገኖ
　　　በጎጥ በሃይማኖት ፣ ይበልጡን ሸንሽኖ
　　　አብይ ሊያፈርሳት ነው ፣ ጭራሹን በትኖ ።

ለይቶ የማያውቅ ፣ ብስልና ጥሬ
እኔ ካልበላሁት ፣ ልድፋው የሚል ጭሬ
ሁለት እግር ያለው ፣ ቆሞ የሚሄድ አውሬ
ኮትኩቶ ያሳደገው ፣ ቄሮውና ቀሬ
　　　ካንድ ዘር ፣ ካንድ ጎጥ ፣ ባስታጠቀው ጥሬ
　　　ልትወድቅ አፋፍ ላይ ፣ ቆማለች ሀገሬ ።

የሐገር ፍቅር ያለው ፣ ፅኑ በሃይማኖቱ
የአንድነት ምሰሶ ፣ ማገር መሰረቱ
አማራ ነው ብለው ፣ ስለሚገምቱ
ባገር በቀል ባንዳ ፣ ኢትዮጵያን ማጥቃቱ
አማራን አሳደው ፣ ገድለው በሚያግቱ
የጅ አዙር ማናቆር፣ ሰምሮለታል ስልቱ
　　　ዘመቻ ባገር ላይ ፣ በወንድም በህቱ
　　　ማቃጠሉ አይሎ ፣ በቤተ እምነቱ
　　　ግፅል ሆኖ ይታያል ፣ የማፍረስ ሂደቱ ።

መመካት ያልቻሉ ፣ በማንነታቸው
በራስ መተማመን ፣ ያልፈጠረባቸው
ዝቅተኛ ስሜት ፣ ያበለሻሻቸው
የፈጠራ ታሪክ ፣ አቅል ያሳጣቸው
በግፍ በጭካኔ ፣ ተሞልቶ ልባቸው
የጫሩትን እሳት ፣ ይሞቁት መስሏቸው
　　　በትዕቢት ያበጡት ፣ በድንቁርናቸው
　　　ያንቀላፋው እሳት ፣ የጠፋ መስሏቸው
　　　ከቤታቸው ዘልቆ ፣ ላይቀር መንደዳቸው
　　　እንቡር እንቡር አሉ ፣ ልቦና ነስቷቸው ።

ታዛቢው

February 4, 2020